ገብርኄር- የአብይ ጾም ስድስተኛዉ ሳምንት

የአብይ ጾም ስድስተኛ ሳምንት ገብርኄር የሚባል ሲሆን ትርጉሙም ቸር አገልጋይ፤ ታማኝ አገልጋይ ማለት ነው። የዚህን አገልጋይ ታሪክና ታማኝ ያስባለውን ምግባር በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 25 ቁጥር 14-30 ላይ እናገኘዋለን። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ወንጌል ስለታማኙ አገልጋይ ካስተማረው ትምህርት በመነሳት አባታችን ቅዱስ ያሬድ ለዚህ ሰንበት በደረሰዉ መዝሙሩ "መኑ ዉዕቱ ገብርኄር ወምዕመን....?" ሲል ይጠይቃል። "በጎ ሥራ እየሰራ ጌታዉን የሚያገኘዉ ቸርና የታመነ አገልጋይ ማነዉ? ባለዉ ሁሉ ላይ የሚሾመዉ ደግሞም እግዚአብሔር በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለዉ የሚለው ማነው?" ማለት ነዉ። በዚህ ሳምንት የሚሰበከው ምስባክ ይህ ነው፡-

መዝ. 39÷8 ትርጉም፦

ከመ እንግር ፈቃደከ መከርኩ አምላኪየ፥ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ መከርሁ፥

ወሕግከኒ በማዕከለ ከርሥየ፥ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው፥ ዜናኩ

ጽድቀከ በማኅበር ዐቢይ። በታላቅ ጉባኤ ጽድቅህን አወራሁ።

በወንጌሉ ላይ ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደ ሰጣቸው፤ ለእያንዳንዱ እንደ አቅሙ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ። አምስት መክሊትም የተቀበለው ሄዶ ነገዶበት ሌላም አምስት አተረፈ፤ እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ። አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቆፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ። ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው። አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት አስረክቦ። ‹‹ጌታ ሆይ፥ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት ›› አለ። ጌታውም ‹‹መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባርያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ›› አለው። ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ። ‹‹ጌታ ሆይ፥ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍኩበት›› አለ። ጌታውም ‹‹መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታ ደስታህ ግባ›› አለው። አንድ መክሊት የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ። ‹‹ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤እነሆ፥ መክሊትህ እነሆ›› አለው። ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው፡- ‹‹አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ ካልዘራህበት እንዳጭድ ካልበተንህበትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤..... የማይጠቅመውንም ባሪያ 'በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል´ እንዳለ የሚያሳስብ ነዉ። ባለ ጸጋ የተባለው ጌታ ነው። መክሊት የተባለው ደግሞ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ስጦታ ነው። በሶስቱ አገልጋዮች የተመሰልን ደግሞ የክርስቶስ አካላት የተባልን እኛ በቤተ-ክርስትያን ዉስጥ በልዩ ልዩ አገልግሎት የምንሳተፍ ምዕመናን ስንሆን ለእያንዳንዳችን የተለያየ ስጦታ ተሰጥቶናል፤ እንደየአቅማችን አምስት፣ ሁለት እና አንድ መክሊት። በዚህ በተሰጠን ስጦታ ልናገለግልበት ያስፈልጋል። ያተረፉት በሚገባ በታማኝነት ያገለገሉ ቅዱሳን ሰዎች ሲሆኑ መክሊቱን የቀበረው ደግሞ በታማኝነት በተሰጠው ጸጋ ማገልገል ሲገባው ያላገለገለ ሰው ነው። በአምስተኛው ሳምንት /በደብረ-ዘይት/ ጌታ እንደሚመጣ ሲመጣ ደግሞ ለሁሉም እንደየስራዉ እንደሚከፍል ተምረናል አሁንም ነገሩን አጽንኦት ሲሰጥ "ጌታቸው ሊቆጣጠራቸው መጣ" በማለት ጌታችን በዕለተ ምጽአት ለኹሉም በሠራው ምግባር መጠን ዋጋ ለመስጠት እንደሚመጣ ያሳስበናል። የታመኑትን አገልጋዮች ሁለትም ያትርፉ አምስት ስለድካማቸዉ አብዝቶ እንደሚከፍላቸው ከወንጌሉ እንማራለን ‹‹መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝ ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታ ደስታህ ግባ›› ። ነገር ግን በተሰጠዉ ጸጋ የማያገለግል ሁሉ ደግሞ ሃኬተኛ ባሪያ-የኃጥአንም ምሳሌ ነዉ። የዚህ ሰዉ ጥፋቱ ለማትረፍ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን የተሰጠዉን መክሊት መቅበሩ ነዉ፤ በዚህም ሳያበቃ ይህ ሰው አለመስራቱ ጥፋት መሆኑን አምኖ መመለስ ሲገባው ጌታውን "ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበት ምትሰበስብ" እያለ ሲወቅስ እናገኘዋለን። እኛንም በጥፋታችን እግዚአብሔርን ከመውቀስ ይልቅ በንስሃ መመለስን ያድለን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

በተጨማሪ መክሊት ቃለ እግዚአብሔር ነው። የሰማነውን ቃለ እግዚአብሔር ለሌላው ማሰማት ይገባናል ። ከእኛ የሚጠበቀው ማሰማቱ ብቻ ነው፤ በልቦና አድሮ ሥራን የሚሠራ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነውና። በአጠቃላይ በዚህ ሳምንት የሚሰጡ ትምህርቶች መሰረታዊ ዓላማቸዉ ክርስቲያኖች ሁላችን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ከካህን እስከ ምዕመን በታማኝነትና በቅንነት ሆነን በተሰጠን መክሊት እንድናተርፍበት ሰላሳ፣ ስድሳና መቶ ያማረ ፍሬ እንድናፈራበት እንጂ ዘመናችንን በከንቱ ንዝህላልነት እንዳናሳልፍ መምከር ማስተማር ነው። ስለዚህ ባለመክሊት የተባልን ምዕመናን በተሰጠን ጸጋ ወጥተን ወርደንን፤ ጾመን ጸልየንን፤ ሃይማኖታችንን አጽንተን እና ምግባራችን አቅንተን በመክሊታችን ልናተርፍ ይገባል። ሩቅ ሀገር ወደ ተባለ ወደ ሰማየ ሰማያት በክብር ያረገው የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በኋለኛው ዘመን ተመልሶ ዓለምን ለማሳለፍ ለእያንዳንዱ እንደሥራው ሊከፍል በክብር ሲመጣ ሁላችን በተሰጠን ጸጋና መክሊት አትርፈን እንድንገኝ "እናንተ መልካም አገልጋዮች ወደ አባቴ መንግስት በሐሴት ግቡ" የሚለውን የሕይወት ቃል እንድንሰማ እሱ ባለቤቱ መድኃኔዓለም ይርዳን! አሜን!!!።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!!!